## ለቡድን መሪዎች የተሰጡ የግምገማ ጥያቄዎች

## እንደ ቡድን መሪ ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 1-27 የተገለጹትን ተግባራት ምን ያህል እንደምታከናውን በእያንዳንዱ ተግባር አጠገብ ከ1-5 ከተሰጡ ቁጥሮች ጻፍ።

1. አድርጌ አላውቅም
2. አልፎ አልፎ
3. አንዳንዴ
4. በተከታታይ
5. ሁል ጊዜ

1. ልክ በ2፡00 ሰዓት እመጣለሁ፣በ3፡30 እሄዳለሁ።__________
2. ወደ ቀኑ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከመሄዳችን በፊት የቡድኑ አባላት እንዴት እንደሰነበቱ እጠይቃለሁ።__________
3. የቡድኑ አባለት የፀለዩት ፀሎት መልስ አግኝቷል።__________
4. የቡድኑ አባላት እርስ በርስ ይረዳዳሉ።__________
5. ለወደፊት በእኔ ቦታ ሆኖ ቡድኑን ሊረዳ የሚችል ሰው እሰለጥናለሁ።__________
6. አንድን ረዳት እንዴት እንደምመርጥና እንደማሰለጥን አውቃለሁ።__________

7. በሳምንቱ መካከል አባላትን በአካል እጎበኛለሁ፣ወይም በስልክ ደህንነታቸውን እጠይቃለሁ።__________
8. ያልመጡ አባላትን እጠይቃለሁ።__________
9. በሳምንቱ መካከል ለአባላት እፀልያለሁ።__________
10.ለቡድኑ አባላት፡- እንዲፀልዩ፣ታሪክ እንዲናገሩ የመሳሰሉትን ነገሮች አደርጋለሁ።__________
11.አባለት በታማኝነት ይመጣሉ፣በታማኝነት ይሳተፋሉ?__________
12. የቡድናችን አባላት እርስ በርስ ጥሩ ጊዜ ያሳልፋሉ።__________
13. ተዘጋጅቼ እመጣለሁ።__________
14. የቡድኑ አባላት ሁሉም ተዘጋጅተው ይመጣሉ።__________
15. ለቀጣዩ ሳምንት እንዲመራ ተራ የተሰጠው ሰው ተዘጋጅቶ ይመጣል።__________
16. ይህ ተራ የደረሰው መሪ ሲመራ አገመግማለሁ፤ከቡድኑ ጋር እወያያለሁ።__________
17. የቡድኑ አባላት መልስ ሲመልሱ አይሸማቀቁም።__________
18. የእያንዳንዱን አባል ስምና ስለ ሕይወቱ በተወሰነ ደረጃ አውቃለሁ።__________
19. የአባላትን መንፈሳዊ ዕድገት ደረጃ አውቃለሁ።( ሕፃን፣ልጅ፣ጎልማሳ፣አዋቂ)__________
20. አንድ አባል ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እንዴት መሸጋገር እንደሚችል እረዳዋለሁ።__________
21 አባላት ሲናገሩ አደምጣለሁ።__________
22. ብዙ እናገራለሁ።__________
23. የቡድንህን አባላት ታስተምራለህ ወይስ የጋራ ውይይት ታደርጋለህ?__________
24. የግል ችግር ሲኖረኝ ለቡድኑ አባለት አካፍላለሁ፤ታሪክም እናገራለሁ።__________
25. እርስ በርሳችን ጠንካራ ጎኖችንና ደካማ ጎኖችን ለይተን አንዳችን አንዳችንን እናበረታታለን።
__________
26. አዳድስ ሰዎችን ወደ ቡድናችን እጨምራለሁ።__________
27. በአባላት ሕይወት ለውጥን አያለሁ።__________

### የውይይት ጥያቄዎች

1. እያንዳንዱ አባል በንኡስ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ሕብረት ተሳትፎ እንዲያደርግ እንዴት ትረዳለህ?
2. ስለ ቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ሕብረት አሠራር ምን አስተያየት አለህ?
3. ከቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ሕበረት ምን ጥቅም አገኘህ?
4. የደቀመዝሙር ማድረግ ሂደት ደረጃ እንዴት ታያለህ?